# የዝግ ዑደት የቴሌቪዥን ካሜራዎች

**Seattle Police Department**

## ቴክኖሎጂው ምንድን ነው?

Seattle Police Department (SPD፣ የሲያትል ፖሊስ መምሪያ) የወንጀል ተግባርን ለመከላከል እና ለመለየት የዝግ ዑደት ቴሌቪዥን (CCTV) የካሜራ ስርዓትን እንደ ሃሳብ ያቀርባል። የ CCTV ካሜራ ስርዓቶች የጦር መሳሪያ ሁከት፣ ህገወጥ የሰው ዝውውር እና ቋሚ የህግ ጥሰት በተደጋጋሚ በሚከናወንባቸው ልዩ ቦታዎች ላይ እንዲተከሉ ሃሳብ ቀርቧል። ካሜራዎቹ ዕይታቸውን ወደ መንገዶች፣ የእግረኛ መንገዶች፣ እና ሌሎች የህዝብ ስፍራዎች ያደርጋሉ እንዲሁም ካሜራዎች እንዳሉ የሚያሳዩ ምልክቶች ይለጠፋሉ። እንዲሁም በግለሰብ የሚተዳደሩ የደህንነት ስርዓቶች የህዝብ



## ቴክኖሎጂውን ለምን እንጠቀማለን?

CCTV የካሜራ ስርዓቶች የነፍስ ግድያዎች፣ ጥቃቶች እና ሌሎች ከባድ የህግ ጥሰቶችን ጨምሮ ከባድ እና ኃይለኛ ወንጀሎች ጋር የተያያዙ ማስረጃዎችን በመሰብሰብ ረገድ መርማሪዎችን ያግዛሉ። የ CCTV ስርዓት ተጠርጣሪዎችን በመለየት፣ ንጹህ የሆነውን ነጻ በማድረግ፣ ከመንገዶች ላይ ነፍስ የሚያጠፉ የጦር መሳሪያዎችን በማስወገድ፣ ከዚህም የተነሳ ህብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት በመቀነስ ረገድ መርማሪዎችን ሊያግዝ ይችላል።

ይህን ቴክኖሎጂ በተመለከተ ክፍት የአስተያየት መስጫ ጊዜ በአሁኑ ሰዓት እየተካሄደ ነው። አስተያየቶችን ለ **Seattle.gov/Surveillance** ማቅረብ ይችላሉ።

ሁሉም አስተያየቶች ይህን ቴክኖሎጂ በሚመለከት በተዘጋጀው Surveillance Impact Report (የክትትል ተፅዕኖ ሪፖርት) ውስጥ ይካተታሉ እንዲሁም ለከተማው ምክር ቤት ይገባሉ።

ከክፍት የአስተያየት መስጫ ጊዜው ውጪ ግብረመልስ ማቅረብ ከፈለጉ፣ https://seattle.gov/council ላይ የሚገኙትን ኢሜይሎች በመጠቀም ለከተማው ምክር ቤት በቀጥታ እባክዎ ያስገቡ።

## አሰባሰብ

የ CCTV ውሂብ የወንጀል ማስረጃ እስካልያዘ ድረስ ቢበዛ ለ 30 ቀናት ስርዓቱ ውስጥ በጊዚያዊነት ይቀመጣል ከዚያም የ SPD ደህንነቱ የተጠበቀ የኤሌክትሮኒክ ማስረጃ ማስቀመጫ ውስጥ ይቀምጣል። SPD ፖሊሲ 7.010 የማስረጃ ማስገባት ሂደትን ያስተዳድራል እንዲሁም ሁሉም የተሰበሰቡ ማስረጃዎች በ General Offense Report (አጠቃላይ የህግ ጥሰት ሪፖርት) ውስጥ ተሰንደው እንዲቀመጡ ያስገድዳል።

## ጥቅም

የ CCTV ፕሮግራም ወንጀል በተደጋጋሚ በሚፈጸምባቸው ልዩ ቦታዎች ላይ ቋሚ የህግ ጥሰት ባህሪ፣ የጦር መሳሪያ ወንጀል፣ እና ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል እና ለመለየት ማስረጃን መሰረት ያደረጉ እና የኢንዱስትሪውን ደረጃ የጠበቁ ቴክኖሎጂዎችን ጥቅም ላይ በማዋል ያልተገመተ ጥበቃን እና የሰራተኞች እጥረትን የሚያስከትሉ ምርመራዎችን ለመቀነስ ያለመ ነው። የታቀዱት የስምሪት ቦታዎች በAurora Avenue North፣ Belltown፣ ቻይናታውን-ብሔራዊ ዲስትሪክት፣ የስታዲየሙ ዲስትሪክት፣ Garfield High School፣ the Capitol Hill የማታ ህይወት ዲስትሪክት፣ እና ዳውንታውን የንግድ ማዕከል ላይ ናቸው።

## ጥበቃዎች

ባለማወቅ የሚደረጉ የውሂብ አሰባሰቦችን ለመቀነስ፣ የ CCTV ካሜራዎች የግላዊነት ምክንያታዊ እሳቤ በማይኖርባቸው ህዝባዊ አካባቢዎች ውስጥ በግልጽ የሚደረጉ ኩነቶችን የሚቀርጹበት ቦታ ላይ ይቀመጣሉ።

የ CCTV ቪዲዮ ቅጂዎች የተቀረጸው ምስል በወንጀል ምርመራ ውስጥ እንደ ማስረጃ ካልተያዘ በስተቀር ከ 30 ቀናት በኋላ ይወገዳሉ። በተጨማሪም፣ የ CCTV ካሜራ ስርዓቶች Office of the Inspector General for Public Safety (በህዝብ ደህንነት መርማሪ ጄኔራል) ቢሮ በማንኛውም ሰዓት ሊታዩ የሚችሉ ሙሉ የተግባራት ዝርዝር ኦዲት ይኖራቸዋል።

City of Seattle